Temari.et

# Environmental Science, 2015 EC, Grade 6 model exam, Yeka

Grade 6 · Environmental Science · 2015 E.C.

**Time allowed:** 120 minutes **Questions:** 49 **Total marks:** 49

Name ______________ Grade ______ ID No. ______ Date ______

**1.** ከሚከተሉት ዉስጥ ኢትዮጲያ የምትገኝበት የአፍሪካ ቀጠና የቱ ነዉ? (1)

**A.** ሰሜናዊ አፍሪካ
**B.** መካከለኛዉ አፍሪካ
**C.** ምዕራባዊ አፍሪካ
**D.** ምስራቃዊ አፍሪካ

**2.** ስለምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ትክክል የሆነዉ የቱ ነዉ? (1)

**A.** ፍፁማዊ መገኛዉ በአፍሪካ ካርታ ላይ ከ18°ሰሜን እስከ 27° ደቡብ ኬንትሮስ ይገኛል
**B.** ፍፁማዊ መገኛዉ በአፍሪካ ካርታ ላይ ከ22°ምስራቅ እስከ 51°28’ምስራቅ ኬንትሮስ ይገኛል
**C.** ፍፁማዊ መገኛዉ በአፍሪካ ካርታ ላይ ከ18°ደቡብ እስከ 27° ሰሜን ኬክሮስ ይገኛል
**D.** በአፍሪካ አህጉር መካከለኛዉ ክልል ይገኛል

**3.** የአንድን ሀገር መገኛ በልዩ ልዩ አቅጣጫ ከሚያዋስኑ ነገሮች ጋር በማነፃፀር የምንጠቀምበት ዘዴ የቱ ነዉ? (1)

**A.** ኬንትሮስ
**B.** ፍፁማዊ መገኛ
**C.** ኬክሮስ
**D.** አንፃራዊ መገኛ

**4.** ከሚከተሉት ዉስጥ አንፃራዊ መገኛ የማይገለፅበት የቱ ነዉ? (1)

**A.** ደቡብ
**B.** በዲግሪ
**C.** ምዕራብ
**D.** ሰሜን

**5.** ከሚከተሉት ዉስጥ አግድም መስመሮችን የሚገልፃዉ የቱ ነዉ? (1)

**A.** መሬትን በሰሜናዊና በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ይከፍላሉ
**B.** መሬትን በምስራቅና በምዕራብ እኩል ይከፍላል
**C.** መነሻቸዉ ግሪንዊች ሜሪዲያን ነዉ
**D.** ከሰሜን ወደ ደቡብ የተሰመሩ የሐሳብ መስመሮች ናቸዉ

**6.** በካርታ ወይም በሉል ላይ ከሚታዩ ዐብይ ትይዩ መስመሮች በትክክል ከዲግሪዉ ጋር የተጣመረዉ የቱ ነዉ? (1)

**A.** የካንሳር መስመር - 231/2°ደቡብ
**B.** የካፕሪኮርን መስመር - 231/2°ደቡብ
**C.** የምድር ወገብ - 90°
**D.** የአርክቲክ ክበብ - 661/2°ደቡብ

**7.** አግድም መስመሮች ከቋሚ መስመሮች በምን ይለያሉ? (1)

**A.** ከሰሜን ወደ ደቡብ የተሰመሩ የሐሳብ መስመሮች ናቸዉ
**B.** መሬትን በሰሜናዊና በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ይከፍላሉ
**C.** በአጠቃላይ 360 ናቸዉ
**D.** መነሻቸዉ ግሪንዊች ሜሪዲያን ነዉ

**8.** ስለ 0° ኬክሮስ እና 0° ኬንትሮስ ትክክል ያልሆነዉ የቱ ነዉ? (1)

**A.** በምድር ወገብ እና በግሪንዊች ሜሪዲያን ላይ መሆኑን ያሳያል
**B.** የአግድምና የቋሚ መስመሮችን ማዕዘናዊ ርቀት ያሳያል
**C.** ፍፁማዊ መገኛን ይገልፃል
**D.** አንፃራዊ መገኛን ይገልፃል

**9.** ከሚከተሉት ዉስጥ የምስራቅ አፍሪካ መገኛ ጥቅም የሆነዉ የቱ ነዉ? (1)

**A.** በትልልቅ ዉሃማ አካላት መከበባቸዉ በቀላሉ በቅኝ ገዥዎች እንዲወረሩ አስተዋፅኦ ያደርጋል
**B.** በምጣኔ ሀብት ዕድገት እንዳያሳድጉ ያደርጋቸዋል
**C.** ባላቸዉ የወደብ አገልግሎት ጠንካራ የንግድ ትስስር እንዲኖራቸዉ ያደርጋል
**D.** የባህር በር የሌላቸዉ ለከፍተኛ የየብስ ትራንስፖርት ወጪ ይዳረጋሉ

**10.** ከሚከተሉት ዉስጥ የምስራቅ አፍሪካ አጎራባች ሀገር የሆነችዉ ሀገር የቷ ናት? (1)

A. ሪዩኒየን
B. ሩዋንዳ
C. ኬንያ
D. ስዊዚላንድ

**11.** የህንድ ዉቅያኖስ ደሴት ያልሆነችዉ ሀገር የቷ ናት? (1)

A. ሲሸየልስ
B. ቡሩንዲ
C. ኮሞሮስ
D. ሞሪሸየስ

**12.** የታላላቅ ሐይቆች ክልል የሆነችዉ ሀገር የቷ ናት? (1)

A. ሶማሊያ
B. ጂቡቲ
C. ሩዋንዳ
D. ማዳጋስካር

**13.** ከሚከተሉት ዉስጥ የአፍሪካ ቀንድ ሀገር ያልሆነችዉ ሀገር የቷ ናት? (1)

A. ታንዛኒያ
B. ጂቡቲ
C. ሶማሊያ
D. ኤርትራ

**14.** የአፍሪካ ትልቁ ደሴት ማን ይባላል? (1)

A. ሞሪሸየስ
B. ሪዩኒየን
C. ኮሞሮስ
D. ማዳጋስካር

**15.** ከአፍሪካ ረጅሙ ወንዝ የቱ ነዉ? (1)

A. ዛምቤዚ
B. ገናሌ
C. ናይል
D. ሩሹማ

**16.** በኢትዮጲያ ዉስጥ የሚገኛዉ ስምጥ ሸለቆ ከየት እስከ የት ነዉ? (1)

A. ከአፋር - ደቡብ
B. ከኦሮሚያ - አፋር
C. ከእስያ - ሞዛምቢክ
D. ከእስያ - ኢትዮጲያ

**17.** በሁለት የመሬት መሰንጠቅ መካከል ያለዉ ቦታ ወደ ላይ ሲነሳ የተፈጠረ ተራራ የቱ ነዉ? (1)

A. ሜሩ
B. ሩዋንዞሪ
C. ኪሊማንጃሮ
D. ራስ ደሽን

**18.** የኢትዮጲያ ትልቁ ተራራ የቱ ነዉ? (1)

A. ሩዋንዞሪ
B. ኤልጎን
C. ኪሊማንጃሮ
D. ራስ ዳሽን

**19.** የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ በአፍሪካ ብቻ ምን ያህል ኪሎሜትር ርዝመት አለዉ? (1)

A. 5600 ኪ.ሜ
B. 6500 ኪ.ሜ
C. 7200 ኪ.ሜ
D. 2700 ኪ.ሜ

**20.** በኢትዮጲያ ዉስጥ የማይገኘዉ የስምጥ ሸለቆ ሐይቅ የቱ ነዉ ? (1)

A. ዝዋይ ሐይቅ
B. የሻላ ሐይቅ
C. ኪቩ ሐይቅ
D. አባያ ሐይቅ

**21.** የመሬትን ትክክለኛ ምስል ለማየት የሚያስችል መተግበሪያ ምን ይባላል? (1)

A. ጂፒኤስ
B. ጎግል ኧርዝ
C. ጎግል ማፕ
D. ጎግል ካርታ

**22.** ምስራቅ አፍሪካን ከሚያዋስኑ ዉሃማ አካላት መካካል ትልቁ ማን ይባላል? (1)

A. የህንድ ዉቅያኖስ

B. የኤደን ባህረ - ሰላጤ

C. የአትላንቲክ ዉቅያኖስ

D. የፓስፊክ ዉቅያኖስ

**23.** ኦክስጅንና አልሚ ምግቦች ለሰዉነታችን የሚሰራጩበትና ካርቦንዳይ ኦክሳይድ እና ሌሎች ቆሻሻዎች በደም አማካኝነት የሚሄዱበት ሂደት ምን ይባላል? (1)

A. ደም

B. የደም ህዋስ

C. የደም ዑደት

D. የደም ስሮች

**24.** ከሚከተሉት አንዱ የደም ህዋስ አይደለም (1)

A. ቀይ የደም ህዋስ

B. ደም - መልስ

C. ነጭ የደም ህዋስ

D. ፕላትሌት

**25.** ከሚከተሉት ስለ ቀይ የደም ህዋስ ትክክል የሆነዉ የቱ ነዉ? (1)

A. በሽታ ለመከላከል

B. አየር ለማስተላለፍ

C. ደም ለማርጋት

D. ጀርሞች ወደ ሰዉነታችን ሲገቡ ለማጥቃት

**26.** ከሚከተሉት ስለደም ህዋሶች ትክክል ያልሆነዉ የቱ ነዉ? (1)

A. ቀይ የደም ህዋስ- ኦክስጅንን ከሳንባ ተቀብለዉ በመሸከም ለመላ የሰዉነታችን ህዋሶች ያደርሳሉ

B. ነጭ የደም ህዋስ- የበሽታ አምጪ ተህዋሲያንን ወደሰዉነታችን ሲገቡ ለማጥቃት ያገለግላል

C. ፕላትሌት - ሰዉነታችን ሲደማ ብዙ ደም እንዳይፈስ ለማርጋት ይጠቅማል

D. ቀይ የደም ህዋስ - በቁጥራቸዉ ከቀይ የደም ህዋሶች ይበልጣሉ

**27.** የደም ስሮች ተግባር ያልሆነዉ የቱ ነዉ? (1)

A. ደምን ከልብ ወደ ተለያዩ የሰዉነት ክፍሎች ማሰራጨት

B. ደምን ከሰዉነታችን ወደ ልብ መመለስ

C. በሽታን ለመከላከል

D. ደምን በሰዉነታችን ዉስጥ ማጓጓዝ

**28.** ደምን ከተለያዩ የሰዉነት ክፍሎች ወደ ልብ የሚያደርሰዉ የደም ስር ዓይነት የቱ ነዉ? (1)

A. ደም-ቅዳ

B. ደም - መልስ

C. ፕላትሌት

D. ቀጫጭን የደም ስሮች

**29.** ለሰዉነታችን ህዋሶች በጣም ቅርብ የሆነዉ የደም ስር የቱ ነዉ? (1)

A. ደም- ቅዳ

B. ቀጫጭን የደም ስሮች

C. ደም -መልስ

D. ፕላትሌት

**30.** የልብ ትርታን የምናዳምጥበት መሳሪያ ምን ይባላል? (1)

A. ቴሌስኮፕ

B. ማይክሮስኮፕ

C. ስቴቶስኮፕ

D. ፔሪስኮፕ

**31.** ደም ኦክስጂንን የሚቀበለዉ ከየትኛዉ የሰዉነት ክፍላችን ነዉ? (1)

A. ሳንባ

B. ልብ

C. ኩላሊት

D. ጉበት

**32.** ከሚከተሉት የልብ ክፍሎች ተግባር በትክክል ቅደም ተከተሉን የጠበቀዉ የቱ ነዉ? (1)

A. ግራ አቀባይ ልበ-ገንዳ ቀኝ አቀባይ ልበ-ገንዳ ቀኝ ተቀባይ ልበ- ገንዳ ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ

B. ቀኝ አቀባይ ልበ-ገንዳ ግራ አቀባይ ልበ-ገንዳ ቀኝ ተቀባይ ልበ- ገንዳ ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ

C. ቀኝ ተቀባይ ልበ-ገንዳ ቀኝ አቀባይ ልበ-ገንዳ ግራ ተቀባይ ልበ- ገንዳ ግራ አቀባይ ልበ ገንዳ

D. ግራ ተቀባይ ልበ-ገንዳ ቀኝ ተቀባይ ልበ-ገንዳ ግራ አቀባይ ልበ- ገንዳ ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ

**33.** በጉርምስና ወቅት በወንዶች ላይ የሚታየዉ ስነ- ህይወታዊ ለዉጥ የቱ ነዉ? (1)

A. የድምፅ መቅጠን

B. የዘር ፈሳሽ ማመንጨት

C. የዳሌ መስፋት

D. የወር አበባ መታየት

**34.** በሁለቱም ፆታዎች ላይ የማይታዉ ስነ-ህይወታዊ የቱ ነዉ? (1)

A. ፈጣን የሆነ የክብደት መጨመር

B. በብብትና በብልት አካባቢ ፀጉር ማብቀል

C. ፈጣን የሆነ የቁመት መጨመር

D. የትካሻና የደረት መስፋት

**35.** ከሚከተሉት ስለወር አበባ ትክክል ያልሆነዉ የቱ ነዉ? (1)

A. ሴቶች አላስፈላጊ የሆኑ የደም ቆሻሻዎችን የሚያስወግዱበት ተፈጥሮአዊ ክስተት ነዉ

B. በማህፀንና በእንቁልጢ ዉስጥ የሚካሄድ ወርሃዊ ዑደት ነዉ

C. ኮረዳዋ ልጅ መውለድ የማትችልበት የዕድሜ ክልል ነዉ

D. ከ12 – 55 ዓመት ዕድሜ ክልል ዉስጥ በሴቶች ላይ የሚታይ ነዉ

**36.** ሰዎች ለግል ፍላጎታቸዉ በሎሎች ሰዎች ላይ ፆታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳና አስገድዶ መድፈር --------------ይባላል። (1)

A. እንጥል መቧጣጥ

B. ዉርጃ

C. ፆታዊ ጥቃት

D. ጋብቻ

**37.** አየርን ወደ ሰዉነታችን ዉስጥ የምናስገባበት ሂደት ምን ይባላል? (1)

A. ኢ- ምጋት

B. ምጋት

C. ካርቦንዳይኦክሳይድ

D. ኦክስጅን

**38.** አየር ወደ ዉስጥ ስንተነፍስ አየር ወደ ሳንባችን ለመድረስ የሚያልፍባቸዉ አካላት ቅደም ተከተል ሲቀመጡ፡- (1)

A. የአፍንጫ ቀዳዳ ሰርን ድህረ-አፍ አብይ ትንቧ ተገንጣይ ትንቧ ደቂቅ ትንቧ ትንከረት

B. ትንከረት ደቂቅ ትንቧ ተገንጣይ ትንቧ አብይ ትንቧ ድህረ-አፍ ሰርን የአፍንጫ ቀዳዳ

C. ድህረ-አፍ ሰርን ተገንጣይ ትንቧ አብይ ትንቧ ደቂቅ ትንቧ ትንከረት የአፍንጫ ቀዳዳ

D. ሰርን ድህረ-አፍ አብይ ትንቧ ደቂቅ ትንቧ ትንከረት ተገንጣይ ትንቧ የአፍንጫ ቀዳዳ

**39.** ለኦክስጅንና ለካርቦንዳይኦክሳይድ ወደ ደም ዉስጥ መግቢያና መዉጫ ሆኖ የሚያገለግለዉ የመተንፈሻ አካል የቱ ነዉ? (1)

A. አብይ ትንቧ

B. ድህረ - አፍ

C. ትንከረት

D. ደቂቅ ትንቧ

**40.** ከሚከተሉት ዉስጥ የመተንፈሻ አካሉ እና ተግባሩ የማይገነኘዉ የቱ ነዉ? (1)

A. ሰርን - አየር ያሞቃል፣ቆሻሻንና ጀርምን ያጣራል

B. ደቂቅ ትንቧ - አየር ወደ አየር ትንከረት መግቢያና መዉጫ ሆኖ ያገለግላል

C. ድህረ - አፍ -የአየር መግቢያና መዉጫ ነዉ

D. ተገንጣይ የአየር ቧንቧ - ከዐብይ ትንቧ ወደ ሳንባ ለሚገባዉና ለሚወጣዉ መዉጫ ሆኖ ያገለግላል

**41.** የስርዓተ ትንፈሳ ጠቀሜታ ያልሆነዉ የቱ ነዉ? (1)

A. ለማዉራትና ለማሽተት

B. የልብ ትርታን መለካት

C. ኦክስጂንን ለህዋሶቻችን ማሰራጫት

D. ሙቀትና ቅዝቃዜን ለማመጣጠን

**42.** ከሚከተሉት ዉስጥ ስለ ስርዓተ ትንፈሳ ሂደት ትክክል የሆነዉ የቱ ነዉ? (1)

A. በአፍንጫ ከመተንፈስ ይልቅ በአፍ መተንፈስ ይመረጣል

B. ድልሺ ወደታች ሲወርድ የደረት ወና ስለሚጠብ የአየር ግፊት ይጨምራል

C. ድልሺ ወደታች ሲወርድ የደረት ወና ስለሚሰፋ የአየር ግፊት ይቀንሳል

D. ድልሺ ወደቦታዉ ሲመለስ የአየር ግፊት ይቀንሳል

**43.** ከሚከተሉት ዉስጥ የምጋትና ኢ-ምጋት የአየር ምንዝሮች በመቶኛ በትክክል ያልተቀመጠዉ የትኛዉ ነዉ? (1)

**A.** ናይትሮጂን- 21%፣ 16%
**B.** ካርቦንዳይኦክሳይድ - 0.03% ፣ 4%
**C.** ናይትሮጂን - 78%፣ 78%
**D.** ኦክስጂን - 21%፣ 16%

**44.** ከሚከተሉት ድብልቅን በትክክል የሚገልፀዉ የቱ ነዉ? (1)

**A.** ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ልዩ ቁሶች ኬሚካዊ በሆነ መንገድ መጣመር
**B.** ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ልዩ ቁሶች አካላዊ በሆነ መንገድ መጣመር
**C.** ከመቀላቀላቸዉ በፊትና በኋላ ያላቸዉን ማንነትና ባህሪ መቀየራቸዉ
**D.** ኬሚካዊ በሆነ መንገድ ስለተጣማሩ ምንዝሮቹ ባህሪያቸዉን ይለዉጣሉ

**45.** ከሚከተሉት ዉስጥ የዋህድ - ዘር ባህሪ ያልሆነዉ የቱ ነዉ? (1)

**A.** በድብልቁ ዉስጥ ያሉትን ምንዝሮች በአይን ወይም በአጉሊ መነፅር መለየት አይቻልም
**B.** በድብልቁ ዉስጥ ያሉትን ምንዝሮች በአይን ወይም በአጉሊ መነፅር መለየት ይቻላል
**C.** በአብዛኛዉ ዋህድ - ዘር ድብልቆች ሙሙት ናቸዉ
**D.** የድብልቁ ይዘት ወጥና ተመሳሳይ ነዉ

**46.** ከሚከተሉት ዉስጥ ድብልቅ ያልሆነዉ የቱ ነዉ? (1)

**A.** ወተት
**B.** ውሃ
**C.** ደም
**D.** አየር

**47.** በድብልቅ ዉስጥ የሚገኝ ፈሳሽ ምንዝርን በዝግታ በማንቆርቆር ከሌላኛዉ ካልሟሙ ጠጣሮች ወይም ፈሳሾች የምንለይበት ዘዴ የቱ ነዉ? (1)

**A.** ቀረራ
**B.** ንጥረት
**C.** ጥሊያ
**D.** ትነት

**48.** በቀላሉ ሊተካ ወይም ሊታደስ የማይችል የጉልበት ምንጭ የትኛዉ ነዉ? (1)

**A.** የፀሐይ ብርሃን
**B.** ንፋስ
**C.** የድንጋይ ከሰል
**D.** ዉሃ

**49.** አንድን ነገር ለሁለት ለመክፈል የሚረዳ የቀላል መኪና ክፍል የቱ ነዉ? (1)

**A.** ሸብልቅ
**B.** መፈንቅል
**C.** ሸክርክሪት
**D.** መፍቻ

— END OF EXAMINATION —